# የ'ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ
# በኢትዮጵያ' መጽሕፍ ቅኝት

ርዕስ -'ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ'
የገጽ ብዛት 516 ደራሲ - ገብሩ አሥራት
ገምጋሚ - ታክሎ ተሾመ (አውስትራሊያ)

አቶ ገብሩ አሥራት የሕወሀት መሥራች፤ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ከ 1991-2001 ድረስ የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ እንደነበሩ ይታወቃል። ዛሬ ላይም ሆነው አረና ትግራይ የሚባል ድርጅት አባል መሆናቸው ይነገራል። እንግዲህ እኚህ ሰው ናቸው ሉዓላምዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ ጽፈው ለንባብ ያቀረቡልን። የመጽሐፉ ርዕስ ከምዕራፎችና ከንዑስ ምዕራፎች ጋር አብሮ የሚያጠነጥን በመሆኑ የመረጡት ርዕስ ተገቢ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፤ ወደድኩት። የደራሲ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ በሕወሀት /ወያኔ ታሪክ ላይ የሚያተኩር ሲሆን እንዲሁም የኢትዮጵያን የጥንት የግዛት ደንበር ወሰን፤ በሚገባ ተርከውታል። ከዚህም በተጓኝ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ኋላ ቀር ምክንያትና ለለውጥ የተደረጉ ኩነቶችን ከረጅም ጉዞ ተነስተው አሁን እስካለንበት ድረስ ዋቢዎችን እያጠቀሱ በስፋትና በጥልቀት እየተጓዙ ታሪኩን አስፍረውታል። ገጽ 7-27 በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ ምን ትመስል እንደነበር፤ በሥርዓቱ ላይ የተነሱ ዓመጾች ምን ይመስሉ እንደነበር፤ የለውጥ ፈላጊዎች የትግል አጀማመር፤ የነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ እንቅስቃሴ፤ የተማሪዎች የትግል አነሳስ፤ የጠባብ ድርጅቶች የትግል እንቅስቃሴ፤ ከምን ተነስቶ የት ሊደርስ እንደቻለ በስፋት ሂደውበታል። እንዲሁም በሰሜን የተፈጠሩ ጠባብ ቡድን የሚሏቸው ጀበሃ፤ ሻዕቢያ የመጀመሪያውን ደረጃ ሲይዙ ቀጥሎ ግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ /ግሕህትን ይጠቅሱና አክለውም መኢሶን በ 1960 ዓ.ም መመስረቱንና እንዲሁም በ 1964 ዓ.ም አንጋፋው አገር አቀፍ ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት (ኢሕአድ ጀርመን በርሊን ከተማ መቋቋሙን ያወሳሉ። (ገጽ 28 ፤ 35 ፤ 36 ፤ 39) እውነት ነው፤ በእኔ እይታ ደራሲው የጀመሩትን ርዕስ ሳያዛቡ፤ ላይና ታች ሳይሉ ተርከውታል። እናም የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽሐፍ በእውነት ላይ ተመርኮዞ የተፃፈ ነው እላለሁ። የትግራይ የባህል ቡድን አፈጣጠር ከምን ተነስቶ የት ሊደርስ እንደቻለ አቶ ገብሩ አሥራት በመጽሐፋቸው እንዲህ ይሉናል። "ተሓህት ትጥቅ ትግል ከመጀመሩ በፊት የትግራይ ተወላጆች የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፤ መምህራን፤ የመንግሥት ሠራተኞች በ 1960 ዎቹ መጀመሪያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መጀመሩን ያወሳሉ። አቶ ገብሩ አሥራት ተሓህትን የተቀላቀሉ ገና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ቢሆንም በወጣትነት ዘመናቸው የሆኑትን ሁሉ የማስታሳወስ ችሎታ እንዳላቸው ከትርካቸው መረዳት የሚከብድ አይመስለኝም። ምክንያቱም በትግራይ የባህል ቡድን ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸውን እነ ካሱ ኢላላ፤ አበበ ተሰማ፤ ረዘነ ኪዳኔ፤ ምትኩ አሸብር፤ ደስታ በዛብህ ገብረ መሰል አባይ፤ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩምንና ሌሎችም፤ በሕዋስ ደረጃም የነበሩ መስፍን አማረ፤ መድኅን ኪሮስ፤ ዜናዊ ሐዱሽ፤ እና ሌሎችንም በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል። ከዘጠነኛ ክፍል በኋላም ደራሲው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ እያሉ ከትግራይ ተወላጆች ጋር በሕቡዕ ይሰባሰቡ እንደነበር፤ ግን ትጥቅ ትግል በአጭር ጊዜ ይመሰረታል የሚል እውቀቱ እንዳልነበራቸው ያን ዘመን ተመልሰው ያስታውሳሉ። (ገጽ 40፤ 41 ፓራግራፍ 2 ፤ 3 ) በመሆኑም ደራሲው መጀመሪያ ላይ የነበራቸውን የእውቀት ውስንነትም ሳይሸሽጉ መተረካቸው የደራሲውን ግልጽነት ያሳያል። ነገር ግን በእኔ እይታ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም የንጉሡ ቤተሰብ ሆነው እያለ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመነጠል ከሚንቀሳቀሰው ቡድን ጋር በምን ምክንያት ወገኑ የሚል ጥያቄ ሳያጭርብኝ አልቀረም። ከደራሲው መጽሐፍ መረዳት የቻልኩት የትግራይ ልጆች የባህል ቡድን ጠንሳሾች ህቡአዊ እንቅስቃሴያቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለተግባራዊነቱ ከትግራይ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ተፈላልገው የፈጠሩት ቡድን ከዚህ እለት ጀምሮ ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ነፃ ትግራይን ለመመስረት የሚጓዙበትን ትግል አህዱ ማለታቸውን መጽሐፉ ፍንትው አድርጐ ያስረዳል። አቶ ገብሩ አሥራት ለትግራይ ሕዝብ ነፃ መውጣት ይሰለፉ እንጂ ድርጅታቸው መተዳደሪያ ደንብም ሆነ ፕሮግራም እንዳልነበረው፤ በዘፈቃድ መጓዛቸውንና ከአንድ ዓመት በኋላ ሕገ-ደንብ መዘጋጀቱን ለታሪክ ሲሉ ዘግበውታል። እንግዲህ የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት እንደሚነግሩን ከሆነ የሕወሀት አባላት ለተወለዱበት ለትግራይ ሕዝብ ሲሉ ሁሉም ተቻችለው ለተነሱለት ዓላማ መቆማቸውን ከመጽሐፉ መረዳት ችያለሁ።2 የትግሉ ዓላማ የትግራይ ትግሪኝ ታሪክ በሚል የትግራይን የ 100 መቶ ዓመት ታሪክ የሚቃኝ ጽሁፍ መውጣቱን አቶ ገብሩ አሥራት ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በተሰኘው መጽሐፋቸው በተለየ መልክ የትግራይን ታሪክ እንዲህ ሲሉ አስቀምጠውታል። (ገጽ 47 ፓራግራፍ 2) "አንደኛ በሥልጣን ሁለተኛ በመወላወል፤ ሦስተኛ በውድቀት ዘመን በማለት"። የሥልጣን ዘመን የተባለው 17 ቱን የአጼ ዮሃንስን የግዛት ዘመን የሚያጠቃልል ሲሆን፤ የመወላወል ዘመን ደግሞ ከአጼ ዮሃንስ ሞት በኋላ የነበረውን የራስ መንገሻ ዮሃንስን ዘመን፤ የውድቀት ዘመን የአጼ ምኒሊክ የበላይነት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠበትና ከዚያ በኋላ ያለው ነው። ይህ ዘመን ትግራይ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ውሳኔ ሰጭነት የተገለለችበትና በግፍና በአድልኦ የተሰቃየችበት እንደነበረ ደራሲው በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። (ገጽ 47 ፓራግራፍ 3) ደራሲው ከላይ በተጠቀሰው ብቻም ሳይገቱ ሌላም እንዲህ ሲሉ ይተርካሉ። "የትግራይ ትግርኚ ግዛት ከአጼ ምኒሊክ በፊት የአሁኑን ትግራይንና ኤርትራን በማጠቃለል ራሱን የቻለ ነፃ ግዛት እንደነበር ነው። የአሁኑ ትግራይ በአጼ ምኒሊክ ቅኝ ግዛት ሥር ወድቆ ኤርትራ ደግሞ በጣሊያን ሥር መሆኑን

ይነግሩናል። በዚህ ሁኔታ የትግራይና የኤርትራ አንድነት ይለምልም የሚል መፈከር አንግበው፤ የመጨረሻ ግባቸው ትግራይን ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አላቀው ከኤርትራ ጋር ለመዋሀድ እንደነበር ያትታሉ። (ገጽ 48 ፓራግራፍ 1) የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ ኢትዮጵያ ከተፈጠረች ጀምሮ ምን ትመስል እንደነበር በመጀመሪያ ምዕራፍ አንድ ላይ የተዋጣለት በእውነት ላይ የተመረኮዘ ትርካ በመሆኑ ብዕርዎን ይባርክ እላለሁ። ነገር ግን ትግራይ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ወይ ብለን ታሪክን ስንመረምር የምናገኘው መልስ በፍጹም አልነበረችም ነው። ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ የትግራይ ልጆች ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፈው ላለመስጠት ደማቸውንና አጥንታቸውን ከስክሰዋል። ብዙ ማስረጃ ሳያስፈልግ እነ አጼ ዮሃንስ፤ እነአሉላ አባ ነጋን መጥቀስ ይቻላል። ይሁን እንጂ ተሐህት አንድ ኢትዮጵያ ማለት አስጠልቶት በትግራይ ብቻ ያጠነጠኑትን ፖለቲካ ዛሬ ላይ ሆነው አቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፋቸው ታሪካዊ ይዘት እንዲኖረው ስህተት ነበር ማለታቸው ምን ያህል ብልህነታቸውን ያሳያል ባይ ነኝ። ከላይ ይህን ካልኩ ዘንዳ አቶ ገብሩ አሥራት ስለ ኢሕአፓም ተርከዋል። "በሰሜን ኢትዮጵያ ይሁን በመላው ኢትዮጵያ በተማሪው፤ በምሁሩና በሌላው የኅብረተሰብ ክፍል የነበረው ድጋፍ እጅግ ከፍተኛ እንደነበር ነው። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ኢሕአፓ እንዴት እንደ ተመሰረተና በየት አካባቢ ትጥቅ ትግል እንደ ጀመረ፤ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የነበረውን ግንኙነት፤ ይከተለው የነበረውን ርዕዮተ-ዓለም ሳይቀር በሚገባ ተርከውታል። ይሁን እንጂ ይላሉ ደራሲው ኢሕአፓ ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅት ቢሆንም በብሔር-ተኮር ድርጅቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዳልነበረው ያምናሉ። ለዚህም ደራሲው በዋቢነት ሕወሀትን፤ ኦነግን በጥርጣሬ ዓይን ይመለከቱት እንደነበር ጠቅሰዋል። ሕወሀት ኢሕአፓን ለማጥቃት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀም እንደነበር ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይሁን እንጂ አቶ ገብሩ አሥራት በቅርበት የሚያውቁትን ሳይሸሽጉ እንዲህ ይሉናል። "ሕወሀት ኢሕአፓ ይወጋኛል የሚል ስጋት ስለነበረው "ቁጥር 7" የሚል ምስጢራዊ መጠሪያ የነበረው ስብሃት ነጋ የኢሕአፓን ይዞታ የሚያጠኑ በርካታ ሰላዮችን ያሰማሩ እንደነበር ነው። በዚህ ምክንያት የኢሕአፓ ሠራዊት መናህሪያ የነበረውን የሰንገደ አካባቢ ወታደራዊ ኃይል ወዘተ በሚገባ አጥንተው መረጃዎችን እየሰበሰቡ ወደ ሕወሀት/ተሐህት መመለሳቸውንና በኋላም ኢሕአፓን ለማጥቃትና ከትግራይ መሬት ማስወጣት እንደቻሉ ነው የሚነግሩን። ለአብነት ያህልም ይላሉ ደራሲው፤ አክሊሉ ማንጁስ ተጫዋችና ቀልደኛ ስለነበር ከኢሕአፓ አመራሮች ጋር መመሳሰል ችሎ ነበር። እነዚህ ሰላዮችም ተሓህትን ከድተን ከኢሕአፓ ጋር ለመታገል ተቀላቅለናል በማለት ሰርገው በመግባት ኢሕአፓን ለማጥቃት እንደረዳቸው ከመጽሐፋቸው መረዳት ችያለሁ። ( ገጽ 53 ፤ 78 ) ነገር ግን ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጎች እኩል የሚደርስ ሆኖ እያለ ተሓህት ኢሕአፓን በትግራይ ወይም በዚህ አካባቢ መንቀሳቀስ የለብህም ማለቱ ተገቢ እንዳልነበረ ደራሲው ዛሬ ላይ ሆነው ስህተቱን ያምናሉ። ኢሕአፓ ከተሓህት በፊት የተደራጀ ቢሆንም እንዴት ሊሸነፍ እንደቻለ ደራሲው ምክንያት የሚሏቸውን እንዲህ ሲሉ ይዘረዝራሉ። "ለኢሕአፓ መዳከም አንዱ ምክንያት በውስጡ የነበረው ችግር እንጂ የተሓህት ወይም የሌሎች ድርጅቶች ጠልፎ የመጣል ችሎታ አልነበረም" ኢሕአፓ የተዳከመው በዋነኛነት በገጠር በደረሰበት ወታደራዊ ሽንፈትና ከተሓህት/ ከሕወሀት ባጋጠመው ፈተና ሳይሆን በአመራሩ ውስጥ በተፈጠረው ቀውስና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ አገናዝቦ ለመምራት ባለመቻሉ ነው ባይ ናቸው ደራሲው። ( ገጽ 53 ፤ 78 79 ) እናም በእኔ እይታ ደራሲው በኢሕአፓና በሕወሀት በኩል የነበረውን ሂደት በትክክል አስቀምጠውታል እላለሁ። በመሆኑም የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ታሪኩን ለማያውቁ ሰዎች በተለይ ለኢሕአፓ አባላት ትምህርት ሊሰጥ እንደሚችል እገምታለሁ።3 ከፍ ሲል ከተጠቀሰው በተመሳሳይ መልክ፤ በሰሜኑ ትግራይ አካባቢ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ድርጅቶች ኢሕአፓ፤ ሕወሀት፤ ሻዕቢያና ጀበሃም ብቻም አልነበሩ። የየካቲትን 1966 ዓ.ም አብዮት ተከትሎ የቀድሞ ባለሥልጣናት የሚመሩት ኢዴህ የተሰኘ ድርጅትም በትግራይ ሽሬ አካባቢ ይንቀሳቀስ እንደነበር አይታበልም። ይህን በተመለከተ አቶ ገብሩ አሥራት እንዲህ ይላሉ።" ኢዴህን ይመሩ ከነበሩት መካከል ጀኔራል መርዕድ መንገሻ፤ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም፤ ጀኔራል ነጋ ተገኝ በዋናነት የድርጅቱ መሪዎች ነበሩ ይላሉ። ( ገጽ 55 ፓራግራፍ 3 ) በወቅቱ እንደታዘብነውና እነደተመለከትነው ከሆነ ሕወሀት በሻዕቢያ እየታገዘ በገዘፈ ቁጥር ሌሎችን ከመታቸው ድርጅቶች መካከል ኢዴህም የሕወሀትን በትር መቅመሱ የታሪክ ሃቅ ነው። ነገር ግን የደራሲው ትረካ ሃቅነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ጀኔራል መርዕድ መንገሻ የኢዴህ መሪ ነበሩ የሚለውን እውነት ብሎ ለመቀበል እቸገራለሁ። ምክንያቱም ጀኔራል መርዕድ መንገሻ በወቅቱ አልነበሩምና ነው። ምናልባት ሲጽፉ በኮፒተር ስህተት ምክንያት ያለ ቦታው ስማቸው ወደ ዚህ ገጽ መጥቶ ሊሆን ስለሚችል ደራሲው ተመልሰው ቢያዩት የተሻለ ይመስለኛል። ለምን ቢሉ የኢዴህ ሊቀመንበር የነበሩት ጀኔራል እያሱ መንገሻ በ 1981 ዓ.ም ለንደን ላይ- አግኝቻቸው፤ "ኢዴህ ተሓትን ከመጋፈጥ ይልቅ ለምን በሌሎች አካባቢ ሆኖ የደርግን ኃይል አልገጠመም ብየ ጥይቄያቸው ነበር በማለት አስፍረውታልና። ( ገጽ 72 ፤ ፓራግራፍ 2 ) አቶ ገብሩ አሥራት ድርጅታቸው በሕወሀት ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን ችግር ወገንተኝነት ሳያሸንፋቸው የችግሮችን መንስዔና ጠንሳሾች እነማን እንደነበሩ ሳይሸማቀቁ፤ አንደበታቸው ይሉኝታ ሳይሸብበው ሂደቱን ነጥብ በነጥብ እያነሱ በስፋት ሂደውበታል። እንዲሁም የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት ድርጅቱን ሲቀላቀሉም ሆነ የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ እያሉ የስሯቸውን ተግባራት ግምት ውስጥ በማስገባት በጐና መጥፎ የሚሏቸውን በጥሩ ቃላት ተርከውታል። ከዚህ በተጓዳኝ ኤርትራ በኢኮኖሚ እንድትበለጽግ፤ የእርትራ ቆንሲሎች እሳቸው ከሚያስተዳድሩት ትግራይ ተቀምጠው ሻዕቢያዎች የኢትዮጵያን አንጡራ ሃብት ከአቶ መለስ ጋር ተመሳጥረው ያካሂዱትን ምዝበራ በስፋት አትተውታል። ከሻዕቢያዎች ባልተናነሰ መልኩ ደግሞ የአቶ መለስ አባት አቶ ዜናዊ በአንድ አህያ ብቻ ሲነግዱ የነበሩ፤ በኋላ ከኤርትራዊያን ሻዕቢያ ጋር ተባብረው በኢትዮጵያ ሃብት ሊከብሩ መቻላቸውን ከመጽሐፉ መረዳት ችያለሁ። በተለይም ይላሉ ደራሲው በአቶ መለስ ትዕዛዝ ከኢትዮጵያ ግምጃ ቤት ውስጥ 1.2 ሚሊዮን ብር ለሻዕቢያ መሰጠቱን በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። ( ገጽ

211 ፓራግራፍ 1 ) አቶ ገብሩ አሥራት ትግራይን ያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ ሻዕቢያዎች የኢትዮጵያን ሃብት ቡና፤ ሰሊጥ በክልላቸው አሾልከው ወደ ኤርትራ እንዳይወስዱ ያደረጉት ጥረት ቀላል እንዳልነበር ነው፡፡ አክለውም ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ንብረት አሾልኮ ሊወስድ ሲል 38 ሚልዮን የሚገመት ሰሊጥ እንዲወረስ አድርገዋል። ( ገጽ 212 ፓራግራፍ 2) ስለዚህ በሕወሀት ተፈጥሮ ስለነበረው ችግር፤ ሻዕቢያዎችና የሕወሀት ባለሥልጣናት በተለይ እነ አቶ መለስ ለሻዕቢያ ምን ያደርጉ እንደነበሩ ደራሲው ነገሮችን አፍረጥርጠው ለአንባቢያን በማቅረባቸው መጽሐፋቸው ታሪካዊ ይዘት ሊኖረው እንደሚችል እገምታለሁ። የተሓህት አመራር ጥቅም ላይ አውሎት የነበረውን ጥቁርና ቀይ የድርጅቱ ባንዲራ ጥቁሩ ቀለም በቀይ ሲለወጥ፤ ቢጫው ላይ ደግሞ የኮከብ ምስል እንዲሰፍርበት መደረጉንና ትርጉማቸውንም እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል። "ቀዩ መስዋዕትነት፤ ቢጫ የወደፊት ተስፋ፤ ኮከቡ ዓለማቀፋዊነት ያመላክታል። ይሁን እንጂ ጥቁሩ ቀለም በአባላት መካከል ጥያቄ ተነስቶ የድሮው የትግራይ ባንዲራ ያን ይመስል ነበር በሚል ለአባላት በሽፍንፍን መታለፉን ከመጽሐፉ መረዳት ችያለሁ። ( ገጽ 100 ) ከዚህ ላይ መረዳት እንደቻለኩት የወያኔ አመራር አባላት እውነተኛውን ታሪክ እየበረዙ ተከታዮችን ብቻ ሳይሆን የትግራይን ሕዝብ በሃሰት እያሳሙኑ ከዚህ መድረሳቸው አስገራሚ መሆኑ ነው። ደራሲው 17 ዓመት ሙሉ ታግለው ለሥልጣን ከበቁና ከሕወሀት አመራር ጋር ሳይግባቡ ከድርጅቱ ከተሰናበቱ በኋላ የሰሯቸውንና ድርጅቱ የተሳሳተ መሆኑንና ትግራይ የራሷ ባንዲራ ነበራት የሚል ማረጋገጫ አለማግኘታቸውን ሲተርኩ ምን ያህል እውቀት እንደነበራቸው መረዳት አይከብድም። ይሁን እንጂ እርሳቸውና ድርጅታቸው ወያኔ የተሳሳተ አቋም ማራመዱን ለታሪክ ሲሉ እውነቱን ዘግበውታል ማለት ይቻላል። ለምን ቢሉ ያለፈ መጥፎ ትዝታ ቢያስቆጭም ወደፊት ሌላ ጥፋት እንዳይከሰት ሌሎች ድርጅቶች ሊማሩበት ይችላሉና ነው። የሕወሀትና የኢሕዴን ግንኙነት በተመለከተ አቶ ገብሩ አሥራት እንዲህ ሲሉ አስቀምጠውታል።" በ 1970 ዓ.ም ከኢሕአፓ ጋር በተደረገው ጦርነት ሁለት ተማርከው ነበር። ስለዚህ አገር አቀፍ ድርጅት እንዲመሰርቱ ተጠየቁ፤ ለዚህ ፕሮጀክት ከተመረጡት መካከል አንዱ በጦርነት ቆስሎ የተማረከ በተሕሀት ህክምና ተደርጐለት ወደ ፖለቲካው የገባ አንዳርጋቸው ጽጌ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ /ኢሕአን/ Ethiopian people`s Revolutionary Movment /EPRM/ መሰረተ። ነገር ግን ድርጅቱን በውጭ እናስተዋውቅ በሚል ወደ ሱዳን ሂደው በዛው ቀሩ እነ አንዳርጋቸው። (ገጽ 135) በኋላም ከኢሕአፓ የተገነጠለው ቡድን ከበለሳ ተነስቶ ወደ ሕወሀት ገባ። ከዛም እነ ታምራት ላይኔ ያሉበት ቡድን ኢሕዴንን መሰረተ ይላሉ። ከኢሕአፓ ያፈነገጡ ግለሰቦች / ቡድኖች ኢሕዴንን ሲመሰርቱ እንዳለ የሕወሀትን ፕሮግራም በመቀበል ነው። የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽ He ፍ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት በግራሞት "ሕወሀት ሳያውቅ 4 የሻዕቢያንና የጀበሃን አቋም ቢደግፍም ከኢሕአፓ የተገነጠሉት እነ ታምራት ላይኔ በቀላሉ የሻዕቢያን አቋም ተቀበሉት" በማለት አስፍረውታል። እንደገናም ደራሲው ተመልሰው የሕወሀትን አቋም ባይቀበሉ ኖሮ አብረው መዝለቃቸው አጠራጣሪ ነበር ሲሉ ገልጸውታል። ( ገጽ 136 ፓራግራፍ 2) ከፍ ሲል የተጠቀሰው ታሪክ እውነቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ ነገር ግን ደራሲው ሕወሀት ሳያውቀው የሻዕቢያንና የጀበሃን አቋም ኢሕዴን ተቀበለው የሚሉት ትክክል አይመስለኝም። ምክንያቱም በመጽሐፋቸው ዙሪያ የኤርትራን የቅኝ ግዛት ጥያቄ ገና ትጥቅ ትግል ሳይጀምሩ ደርጅታቸውም ሆነ እርሳቸው መደገፋቸውን በስፋት ዘግበውት እያለ እኛ ሳናውቅ የደገፍነውን ኢሕዴን የሻዕቢያን አቋም ደገፈ ማለታቸው ተገቢ መስሎ አልታየኝም። የሉዓላምዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት ከፍ ሲል በመጽሐፋቸው ያሰፈሩትን በሚፃረር መልክ በድልና በመስዋዕትነት የደመቀው የኢሕዴን ሠራዊት ታሪክ መጽሐፍ ደራሲ ጀኔራል አክሊሉ አሳየ ሕዳር 2003 ዓ.ም በፃፉት መጽሃፋቸው እንዲህ በማለት ያወሳሉ። "ትግራይ እንደገባን ትጥቃችን እንድንፈታ ሕወሀት መመሪያ አስተላለፈ ይላሉ። (ገጽ 47 እና ገጽ 96 ) አክለውም በድልና በመስዋዕትነት የደመቀው የኢሕዴን ሠራዊት ታሪክ መጽሐፍ ደራሲ ጀኔራል አክሊሉ አሳየ በ 2003 ዓም ባሳተሙት መጽሐፋቸው ከበለሳ ተነስተን ትግራይ ስንሄድ በሕወሀት ላይ እምነት ኑሮን አይደለም፤ እንዲሁም ሕወሀቶች ጭልጥ ያሉ ፀረ-ዴሞክራቲክ ናቸው፤ ሕወሀቶች ያስሩናል፤ ይገድሉናል የሚል ሥጋት ነበረን በማለት በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። ( ገጽ 220 ፤ 317 ፓራግራፍ 2 ) ስለሆነም እንዲህ የተለየ ሃሳብ ባለበት ሁኔታ ኢሕዴን ሳያቅማማ የሻዕቢያን የመገንጠል ጥያቄ ተቀበለው የሚለውን የአቶ ገብሩ አሥራትን አባባል አምኖ ለመቀበል የሚያስቸግር ይመስለኛል። ምክንያቱም ኢሕዴን ሕወሀትን ስንቀላቀል እንታሰራለን ብለን ፈርተን ነበር ካሉ ሊኖራቸው የሚችለው አማራጭ የሕወሀትን ፕሮግራም መቀበል ብቻ ሳይሆን የኤርትራን የቅኝ ግዛት ጥያቄ አሜን ብሎ መቀበል ይመስለኛል። ነገር ግን ኢሕዴን አባላት የኤርትራን የቅኝ ግዛት ጥያቄ አንቀበልም ቢሉ ሕወሀት አያጠፋቸውም ነበር ወይ ብለን ስንጠይቅ የእኔ አመለካከት ህልውናቸው አደጋ ላይ ይወድቅ ነበር ነው። የሓውዜኑ ጭፍጨፋ በተመለከተ፡-የሉዓላምዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት ደርግ የፈጸመውን የሓውዜን ጭፍጨፋ ዓለምን ጉድ አሰኝቷል ይላሉ። (ገጽ 169 ) የደራሲው የታሪክ አወራረድ ምንም እንኳን እውነትነት ቢኖረውም ለሐውዜኑ መጨፍጨፍ የወያኔ እጅ እንዳለበት የሕወሀት ከፍተኛ ሰዎች እነ አቶ ገብረ መድህን አርዕያ በየጊዜው ሲናገሩ ይደመጣሉ። ይሁን እንጂ እልቂቱን የፈጸመ ደርግ እንጅ የሕወሀት እጅ የለበትም ባይ ናቸው አቶ ገብሩ አሥራት። እንዲሁም በ SBS ቀርበው ሲጠይቁም፤ የሕወሀት እጅ ነበረበት የሚባለውን እንደማይቀበሉትና በሌሎችም አካባቢ ደርግ ብዙ እልቂት ማድረሱን አስረግጠው ሲናገሩ ማድመጥ ችያለሁ። ( ጥር 11 / 2015 ዓ.ም ) ስለዚህ የተወሰኑ የሕወሀት አባላት ለሓውዜኑ እልቂት የሕወሀት እጅ አለበት እያሉን ስለሆነ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ የሚለውን ወይስ ሌሎች የሕወሀት አባላት የሚሉትን እንቀበል የሚል ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል እገምታለሁ። ሕወሀት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ሰርጐ በመግባት ምን ሚና ይጫወት እንደነበር የደራሲውን ትረካ እንመልከት።" ሕወሀት በሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመንግሥት የፖለቲካና የፀጥታ መዋቅር ውስጥ ሰርጐ ይገባ እንደነበር፤ በሃሰት የሕወሀት አባላት ናቸው እያሉ በምስጢር ከእነ አባይ ፀሃየ

ደብዳቤ የተላከ በማለት የሕወሀት ደጋፊ ያልሆኑ ግን ለሕወሀት አስጊ የሚባሉትን በቀይ-ሽብር ያስሙቱና ያሳስሩ እንደነበር ደራሲው በግልጽ አስቀምጠውታል። (ገጽ 159 ፤ 161፤ 169 ) በመሆኑም ሕወሀት በመንግሥት ሰርጎ እየገባ ደርግን ያሳስት ነበር ካሉን ደራሲው፤ በእኔ እመለካከት የሐውዜኑ ጭፍጨፋም የዚሁ አካል እንደነበር መገመት ቢያንስ ነው። ስለዚህ እውነቱን ለመጨበጥ ስለሚያስቸግር የሕወሀት አባላት ለታሪክ ሲሉ ሃቁን ሊነግሩን ይገባል ባይ ነኝ። የሕወሀት የሠላም ጥሪን አስመልክቶ መጋቢት 19 ቀን 1981 ዓ.ም ባለ 8 ነጥብ የድርድር ሃሳብ አቅርቦ ነበር። ይሁን እንጂ ሳይሳካ ቀርቶ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ እንዲገባ አሜሪካ ፈቀደች ይሉናል ደራሲው። (ገጽ 172 ፤ 176 ፤ 181) ከዚህ ላይ አሜሪካ ባትፈቅድስ የሕወሀት እጣፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ደራሲው ያሉት ነገር የለም። እንዲሁም በወቅቱ ተደረገ የተባለው ድርድር አሻጥር የተሞላበት ስለነበር ሕወሀት ለራሱ የመሰለውን ብሄር-ተኮር ድርጅት በተለይ እንደ ኦነግ ካለው ጋር የውስጥ ስምምነት አደረገ እንጂ ከአገራዊ ድርጅቶች ጋር ያደረገው ስምምነት አልነበረም። ለምሳሌ መኢሶን ለመደራደር ልዑክ በርሃ ድረስ ቢልክም የኤርትራንና የብሄረሰቦችን መገንጠል ሊቀበል አልቻለም በሚል ተባሯል። ኢሕአፓም ቢሆን ከድርድሩ እንዳይሳተፍ ነው የተደረገው። ይህን በተመለከተ አቶ መለስ ዜናዊ ከኢሕአፓ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለሚ .ር ፖል እንዲህ ብለዋል። ግንኙነታችን ጥሩ አይደለም፤ ኢሕአፓ የአማራውን የበላይነት ነው የሚፈልጉት"። ( መለስ፤ ሲአይኤ እና ኢትዮጵያ ሉሉ ከበደ ክፍል 2 ) ታዲያ ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ ኢሕአዴግ የትብብር ጥሪ አድርጓል ማለት እንዴት ይቻላል?።5 የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ ደራሲ ኢትዮጵያ የባሕር በር ማጣቷና የአሰብ ወደብ ተጠቃሚ አለመሆኗ ከልብ የመነጨ ቁጭት እንደሚሰማቸው በየጊዜው ከሚናገሩትና ከሚጽፉቸው ጽሁፎች መረዳት ችያለሁ። ለዚህም ይመስላል የአሰብ ወደብ ወደ ኤርትራ መሄድ ከሚያስቆጫቸው ወገኖች ግንባር ቀደም አቶ ገብሩ አሥራት ናቸው ሲባል እሰማለሁ። አቶ ገብሩ አሥራት በኢትዮጵያ ሉዓላዊ ላይ በነበራቸው ጠንካራ አቋም ከእነ አቶ መለስ ዜናዊ ጋርም ከፍተኛ ልዩነት ተፈጥሮ ውዝግብ ውስጥ ገብተው እንደነበር የማይረሳ የትላንት ታሪክ ነው። በመሆኑም ደራሲው በአሰብ ወደብ ላይ ጠንካራ አቋም ስላላቸው በመጽሐፋቸው ውስጥም የሰብን ወደብ አስመልክቶ ያነሱት ነጥብ መጽሐፋቸውን ታሪካዊ ሊያሰኘው ይችላል። ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና በአፍሪካ ከፍተኛ ቦታ እንደነበራት፤ ነገር ግን ጠላቶቿ ባደረጉት ተከታታይ ጥቃት መልሳ ልታጣው ችላለች በማለት አቶ ገብሩ አሥራት ልብ በሚስብ መልኩ ተርከውታል። ይሁን እንጂ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን አስመልሳ ነበር ይሉና፤ ነገር ግን ዛሬ በኢሕአዴግ ዘመን መልሳ ማጣቷን በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። ( ገጽ 473 ) በመሆኑም በእኔ አመለካከት የደራሲው የታሪክ አወራረድ ውብና ድንቅ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ሌላው መደበኛ ሠራዊቱ ወደ ቤተሰቡ ከመቋቋሚያ ጋር መሸኘቱን ሲገልጹ፤ "የቀድሞ ወታደሮችና ተቀናሽ የሕወሀት ታጋዮችን መልሶ ማቋቋም ነበር ይላሉ። በተለይ "ግማሽ ሚልዮን የሚጠጋውን የቀድሞ ሠራዊት። ( ገጽ 195 ) የኢትዮጵያ መደበኛ ጦር መቋቋሚያ እየተሰጠው ተሰናበተ የሚሉትን እውነት ነው ለማለት ይከብደኛል። ምክንያቱም የቀድሞ ነባር የሠራዊት አባላት በየጊዜው እንዲህ ሲሉ ማድመጥ ችያለሁ። "ሕወሀት/ ወያኔ ያሰረውን አስሮ የገደለውን ገድሎ ቀሪው የመንገድ ለማኝ እንድንሆን ፈረድብን ይላሉ"። ይህ እውነተኛ ታሪክ ይመስለኛል፤ ለምን ቢሉ ከጀኔራል እስከ ተራ የሠራዊት አባል ድረስ ብዙዎች መንገድ ላይ ሆነው ሰለ እግዜአብርሄ እያሉ ሲለምኑ ተስተውለዋልና። ስለዚህ ሠራዊቱ መቋቋሚያ እየተሰጠው ያሉት ደራሲው የሕወሀትን ሠራዊት ለማለት ፈልገው ከሆነ እውነት ብሎ ማለፍ ይቻላል። የሉዓላዊነ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት የቀደሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት የኢሕአዴግ ሠራዊት አወቃቀር ምን ሊመስል እንደሚችል እንዲህ ሲሉ አስቀምጠውታል። "የኢሕአዴግ ሠራዊት በአብዛኛው ከሕወሀት አባላት የተመሰረተ ነው ሲሉ፤ ባንፃሩ የቀድሞ ሠራዊት ደግሞ ከደቡብና ከማሀል አገር በተገኙ ዜጐች የተገነባ መሆኑን ይነግሩናል። ( ገጽ 222 ፤ፓራግራፍ 1) እንደሚታወቀው የኢሕአዴግ ሠራዊት የተመሰረተው አብዛኛው ከሕወሀት አባላት ነው ማለታቸው ሃቅን የተንተራሰ ትንታኔ ነው። ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት የተመሰረተው ከሁሉም ብሄር-ብሄረሰቦች ዝንቃዊ ባህሪ እንደነበረው የሚካድ አይመስለኝም። ለምሳሌም ኤርትራዊ እውቅ የጦር መሪ የነበሩ እነ ጀኔራል አማንና ከትግራይም እውቅ የጦር አዛዦች እንደነበሩ ነው። ታዲያ ደራሲው የኢትዮጵያ መደበኛ ጦር ከደቡብና ከመሀል አገር የተገነባነው ሲሉ ምን ማመላከት እንደፈለጉ ግልጽ አይደለም። ይሁን እንጂ ሕወሀት/ኢሕዴግ የቀድሞ ሠራዊቱን መበተኑ ተገቢ እንዳልነበር፤ ከሁለቱ የተውጣጡ አባላት አብረው እንዲሰሩ ቢደረግ ኖሮ የተሻለ ሠራዊት መፍጠር ይቻል ነበር በማለት ዛሬ ላይ ሆነው ደራሲው ቁጭት በተቀላቀለበት ብዕራቸው ታሪኩን በትክክል አስቀምጠውታል። አቶ ገብሩ አሥራት ሕወሀትና ሻዕቢያ የነበራቸውን ታሪካዊ ትስስር በስፋት ሂደው ታሪኩን በመተረካቸው እወነቱን ማወቅ ለሚፈልግ መጽሐፉ ያግዛል ባይ ነኝ። ይሁን እንጂ ግንቦት 1983 ዓ.ም ላይ ኤርትራ በገዛ እጇ ጊዜያዊ መንግሥት መስርታ ከ 2 ዓመት በኋላ ላወጀችው ነፃነት ሕጋዊ ልባስ ለመስጠት ባካሄደቸው የተባበሩት መንግሥታት ታዛቢ በሆነበት ሕዝበ ውሳኔ ነፃነቷን አውጃለች፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም ነፃ እንድትወጣ ፈቅዷል ይላሉ። ( ገጽ 476 ፓራግራፍ 2) ቀደም ሲል አቶ ገብሩ አሥራትም ሆነ ድርጅታቸው ኤርትራ በቅኝ ስለምትገዛ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ለተግባራዊነቱ እስከ መጨረሻው መታገላቸውን ነግረውናል። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ እንደገና ተመልሰው በዚህ ምዕራፍ ላይ ኤርትራ ነፃነቷን በራሷ አወጀች ማለታቸው ታሪኩን ሊያዛባው እንደሚችል እገምታለሁ። ምክንያቱም ሕወሀት ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር እንድትሆን ቅድሚያ የተባበሩት መንግሥታትን ይወተውት እንደነበር ምስጢሩ ለሕዝብ የተሰወረ አይደለምና። የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ እውነተኛ ታሪክን ያካተተ በመሆኑ የድርጅታቸውን ባህሪም እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል። ሕወሀት ሥልጣን ከያዘ በኋላ የሕወሀትን የበላይነት ለማስጠበቅ፤ ሌሎችን ድርጅቶች በመደፍጠጥ የራሱን የበላይነት ማረጋገጥ እንጅ ለዴሞክራሲ፤ ለሕዝቡ መብት መከበር ደንታ እንዳልነበራቸው ነው። ግን ለዚህ ሁሉ አቶ መለስ ዜናዊን ተጠያቂ አድርገዋል። ( ገጽ 226፤ 227 )

እንደሚታወቀው ድርጅት ወይም መንግሥስት የተዋረድ ሥልጣናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለድርጅቶች መደፍጠጥና ለሕዝቡ ጭቆና በተለይ ጠቅላይ ሚስትሩን ብቻ ተጠያቂ ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ባለሥልጣን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የመወሰን ሥልጣን አለውና ሁሉም የተጠያቂነት ድርሻ ሊኖረው ይገባል ባይ ነኝ። ነገር ግን አቶ ገብሩ አሥራት የታሪክ ሰው ለመባል ስህተቱን ስህት፤ እውነቱን እውነት በማለት ያለውንና የነበረውን ታሪክ ለሕዝብ ይፋ በማድረጋቸው ሸክማቸውን አራግፈዋል። ስለዚህ የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ ለሌሎች የሕወሀት አባላት አርዕያ ሊሆን ይችላል ባይ ነኝ።6 የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት ብሄር-ብሄረሰቦችን በተመለከተ በመጽሐፋቸው እንዲህ ሲሉ አስፍረውታል። "በደርግና ከዛ በፊት የነበሩት መንግሥታት በኢትዮያ ስም የብሄር-ብሄረሰቦች መብት መደፍጠጡን፤ ከዛም በኢሕአዴግ ደግሞ በስመ የብሄር-ብሄረሰቦች መብት መከበር ኢትዮጵያዊነትን ደፍጥጧል ባይ ናቸው። (ገጽ 480) ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። እኔ እስከ ማውቀውና እስከገባኝ ድረስ በንጉሡ ዘመን በአንድ ብሄር ላይ ያነጣጠረ የመደፍጠጥ ባህሪ እንዳልታየ ነው። እንዲሁም በደርግ ዘመን የብሄር-ብሂረሰቦች መብት ተከብሮ፤ ከዚህ በፊት ያልተደራጁ የመደራጀት ባህሪ የታየበትና ሁሉም አገሬ ኢትዮጵያ ሲል የተሰተዋለበት ዘመን ነበር። (ተፈጥሮ ያደርስ የነበረውን ድርቅና የባለሥልጣናትን ቢሮክራሲ ግፍ ሳንረሳ ማለት ነው። የደርግ፤ የሕወሀት፤ የመኢሶን፤ የኢሕአዴግና የሌሎች ፖለቲካ እንቅስቃሴ እስከ ዛሬ ድረስ እርስ በርሳችን በመጠፋፋት ላይ እንገኛለን ይሉናል። የደራሲው አባባል እውነት ቢሆንም በፖለቲካ ድርጅቶች በኩል የነበረውን አሰላለፍና አካሄድ በግርድፉ አልፈውታል። ( ገጽ 478 ) እንደሚታወቀው በደርግ ዘመን የነበሩ ፖለቲካ ድርጅቶች ሻዕቢያ፤ ሕወሀት፤ ኦነግ፤ የእንገነጠላለን ጥያቄ ያነገቡ ሲሆን፤ ባንፃሩ መኢሶን፤ ኢሕአፓና ደርግ የሥልጣን ይገባኛል ፖለቲካ ቢያካሂዱም በዋናነት ግን በአገር ሉዓላዊነት፤ በሕዝብ አንድነት የሚያምኑ ስለመሆናቸው መጠራጠር አይቻልም። በመሆኑም ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ ደራሲው "ጠባቡንና ሆደ ሰፊውን ሳይለዩ ሁሉም በማለት" ተርከውታል። ቢሆንም ወደፊት ያለፈው ጥፋት እንዳይደገም የትግሉ እንቅስቃሴ በምን መልክ መካሄድ እንዳለበትና ለአገሪቱ ይበጃል ያሉትን ደራሲው በመጽሐፋቸው ውስጥ አስቀምጠዋል። ስለዚህ የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ በእኔ እይታ እውነተኛ የታሪ መጽሐፍ ነው እላለሁ። የቅኝቱ ማጠቃለያ፡- የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት ወደፊትም ኢሕአዴግ ቢወገድና ሌላ ቢተካ የመጠፋፋቱ ፖለቲካ አያባራም ባይ ናቸው። ከዚህ ችግር ለመውጣት የጋራ እሴትና አስተሳሰብ መገንባት እንዳለበት ሳይመከሩ አላለፉም። የደራሲውን ሥጋት እኔም እጋራዋለሁ። ምክንያቱም ዛሬ በዓይን የሚታየው የፖለቲካ ሂደት ተስፋ ሰጭ አይደለምና ነው። በመሆኑም ደራሲው ችግሮችን ብቻ ሳይሆን መፍትሄ ይሆናሉ የሚሏቸውንም በማመላከታቸው በአንባቢያን ዘንድ መጽሐፋቸው ተወዳጅነት ሊያገኝ እንደሚችል እገምታለሁ። የሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ አቶ ገብሩ አሥራት የልጅነት እድሚያቸውን ያዋሉት ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ነፃ ሪፐብሊክ ትግራይን ለመመስረት፤ ከዚህም በተጨማሪ ኤርትራም ነፃ አገር እንድትሆን 17 ዓመት መታገላቸውን ከመጽሐፋቸው መረዳት ችያለሁ። ስለሆነም ትግላቸው ሰምሮ የትግራይ አስተዳዳሪ እስከ መሆን ደርሰው ነበር። በድርጅታቸው በሕወሀት ውስጥ በተፈጠረው ከፍፍል የነ አቶ መለስ ዜናዊ ቡድን የአንበሳውን ድርሻ ወስዶ እርሳቸውንና ጓደኞቻቸውን ከሚወዱትና ካሳደጋቸው ከሕወሀት መነሳታቸውን አስመልክቶ ያነሱት የነበረውን ክርክር በሚገባ ተርከውታል። እናም እኒህ ሰው ናቸው ዛሬ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደራሲ ባሳለፉት የትግል ጉዞ የሰሯቸውን በነቂስ እያነሱ ታሪኩን አቅርበውልናል። ደራሲው በራስ የመተማመን ባህሪ ስላላቸው፤ ይሉኝታ ሳያሸንፋቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት "ጠንቅ ሆነናል፤ ሁኛለሁ" በማለት የፀፀት ቃላትን አልፈው አልፈው መጠቀማቸውን ስረዳ ራስን የመለወጥ ባህሪ ምን ሊመስል እንደሚችል ግንዛቤ ለመጨበጥ ይቻላል። አቶ ገብሩ አሥራት የይቅርታን አስፈላጊነት ጠንቅቀው የተረዱ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ብዙ ነገሮችን መጽሐፋቸው አካቷል። በቅንጅት ዘመን በ 1997 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ሕዝብ በተሰበሰበበት ለሰሩት ጥፋት ይቅርታ መጠየቃቸው አይዘነጋም። ( ገጽ 432 ) እናም ደራሲው እውቀት ያላቸውና አርቆ አሳቢ ሰው መሆናቸውን መረዳት ችያለሁ። የኢትዮጵያ ጉዳይ የባህር ወደብ፤ አሰብ ወደ ኤርትራ መሄዱ ያንገበግባቸዋል፤ በሕይወታቸው ጥሩ ነገር ማየት ይሻሉ። የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ፤ ዴሞክራሲን ለማስፈን በጋራ አገራዊ ራዕይ ሁሉም መታገል እንዳለባቸው ይመክራል። በእኔ እይታ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሐፍ ቢነበብ፤ ቢነበብ የማይሰለች የተዋጣለት እውነተኛ የታሪክ መጽሐፍ ነው። ሌሎችም ቀሪውንና የጐደለ የሚሉትን፤ ያላፉበትን ታሪክ እንደሚጽፉ መጽሐፉ አርዕያ ሊሆን ይችላል። ከመነሻው እስከ መድረሻው የመጽሐፉን ይዘት እንደተመለከትኩት ከሆነ የአቶ ገብሩ አሥራት መጽሕፍ በእውነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለዚህና ለመጭው ትውልድ ትምህርት ሊሰጥ እንደሚችል እገምታለሁ።7 አቶ ገብሩ አሥራት ያን ሁሉ 17 ዓመት የመከራ ዘመን አልፈው፤ ከዛም ሥልጣን ይዘው፤ እንዲሁም ከሥልጣን ተባረው/ተወግደው/ ያለፈው ቆጭቶዎት ለቤተሰቤና ለአገሬ መጥፎ ታሪክ ተሸክሜ አላልፍም ብለው የእርስዎንም ሆነ የድርጅትዎን ታሪክ በጥሩ አማርኛ አንጥረው እውነተኛ ታሪክ በመፃፍዎ ሊኮሩ ይገባ እላለሁ። ለደራሲው ማሳሰቢያ፡- ገጽ 40- የሚመመሩ/ የሚመሩ/ ገጽ 43- ፓራግራፍ 3 አቢዛኛዎቻችን /ብ ገጽ 56. ፓራግራፍ 2 ተመረጦ/ ጠ ገጽ 149. ውሳኔ፤ ውሳኔ / 2 ገጽ 160.ትላቅ /ታ ገጽ 178.አመባው/ ም ገጽ 212 ግዢው/ ግዢ ገጽ 212 አገኝ/ ኘ ገጽ 243-ላገኘሁ/ ው ገጽ 244.ግዳይ/ ገ ገጽ 326 አካረካሪ/ኪ.ራ ገጽ 410.መሰነንጠቅ በተወሰነ መልክ ድግግሞሽና የዓ.ም ቅደም ተከተል አልፎ አልፎ መጽሐፉ ይታይበታል፤ እንዲሁም የሕትመት ጥራቱ ያን ያህል በመሆኑ ገጾች የመለያየት ባህሪ እያሳዩ ስለሆነ ይታሰብበት እላለሁ።
አስተያየት መስጠት ለሚፈልግ፡-

Taklo. texome@gmail.com Ethiofitih.com/